## እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!

## ማስታወቂያ

### የገንዘብ ማሰባሰቢያ ቅጽ

ለሕንጻ ግዢ የገንዘብ ማሰባሰቢያ የተዘጋጀውን ቅጽ ሞልታችሁ ያልመለሳችሁ ወገኖች እባካችሁ ሞልታችሁ ለዲያቆናት ስጡልን። የህንጻ ኮሚቴ አስተባባሪዎች። እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

### የአርብ ፕሮግራም

የአርብ ፕሮግራም የምጸልይበት፣ የምንንቃቃበትና የምንማርበት ፕሮግራም ነው። የምንችል ሁሉ እንድንካፈል እናበረታታለን። እንዲጸለይላችሁ የምትፈልጉ ወገኖች ለፕሮግራም መሪዎች እንድታሳውቁ እናሳስባለን። ጌታ ይባርካችሁ!

"ወደ ውጭም አውጥቶ፦ ጌቶች ሆይ፥ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? ኣላቸው።
እነርሱም፦ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ አሉት።" (ሐዋ. 16፡ 30-31)

*"በሚመጣው ዘመን ያዕቆብ ሥር ይሰድዳል፥ እስራኤልም ያብባል ይጨበጭብማል፤ በፍሬያቸውም የዓለሙን ፊት ይሞላሉ።" (ኢሳ. 27፡6)*



- ⇒ የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ በምጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?
- ⇒ ማገልገል ይፈልጋሉ?
- ⇒ **Yeec.org App ጭነዋል?**
- ⇒ **http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?**

ሽማግሌዎችን ለማግኘት፦
773-886-0818 (ሲሳይ)
773-865-6102 (ብረሃኑ)
773-507-0194 (ጋሽ አያሌው)
773-910-0485 (ፒተር)
773-961-5332 (ጌቱ)

**መደበኛ ፕሮግራሞች**
እሑድ 1:30 p.m. -- 4:30 p.m.
አርብ 7:00 p.m. -- 9:00 p.m.

| የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን | | Chicago Yemsrach Evangelical Church |
|---|---|---|

"እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ" ሉቃስ 2፡10




"በሰማይ ያለው አባት ለሚለምኑት እንዴት አብልጦ መንፈስ ቅዱስን ይሰጣቸው?"
(ሉቃስ 11፡13)

| Chicago Yemsrach Evangelical Church<br>4455 N. Seeley Avenue<br>Chicago, IL 60625 | መደበኛ ፕሮግራሞች<br>እሑድ 1:30 p.m. -- 4:30 p.m.<br>አርብ 7:00 p.m. -- 9:00 p.m. |
|---|---|
| **August 20, 2017** | **ነሃሴ 15፣ 2009 ዓ.ም.** |

## የእለቱ ፕሮግራም መርሃ-ግብር

| | |
|---|---|
| ጸሎት መሪ................ | ወንድም መኮንን ጂኔሎ |
| አምልኮ...................... | የቤተክርስቲያን አምልኮ ቡድን |
| ፕሮግራም መሪ .......... | ወንድም ሲሳይ መሸሻ |
| ቃል .......................... | ፓስተር ጌታቸው ዶሪ |
| ማጠቃለያ ................ | ፕሮግራም መሪ |

### የሳምንቱ ጥቅስ

"ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው።" (ዮሐ. 1፡12)

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች**

| መሪ | ቀን | አድራሻ |
|---|---|---|
| ወ/ም አያሌው አስፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 6602 N. Damen Ave., Chicago IL 60626 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ማክሰኞ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ዮናስ ባህሩ | ማክሰኞ | 5523 N. Kenmore Ave., Chicago, IL 60640 |
| ወ/ም ሰለሞን ዴሌቦ | ቅዳሜ | 549 Sheridan Rd., Apt. 3, Evanston, IL 60202 |
| ወ/ም መስፍን ጌታቸው | ዕሮብ | 4631 N. Beacon St., Chicago, IL 60640 |

## መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ካሳ

**ጸሎት አስተምረን -- አባታችን ሆይ (ክፍል አንድ)**

*"እርሱም በአንድ ስፍራ ይጸልይ ነበር፥ በጨረሰም ጊዜ ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ፦ ጌታ ሆይ፥ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርቱን እንዳስተማረ እንጸልይ ዘንድ አስተምረን አለው። አላቸውም፦ ስትጸልዩ እንዲህ በሉ፦ በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ ..." (ሉቃ. 11፡1-2)*

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር በነበረው አገልግሎት ትልቅ ትኩረት ከሰጠው ልምምድ መካከል ጸሎት ዋንኛው ነበር። በመጽሐፍ ቅዱሳችን ላይ በብዙ ስፍራ ጌታችን ሲጸልይ ተዘግቧል። ብዙ ጊዜ ከደቀ መዛሙርቱ ተለይቶ ለብቻው እየጸለየ ከአባቱ ጋር ጊዜ ያሳልፍ ነበር። (ማር. 4፡16፤ ሉቃ. 5፡16፤ ማቴ. 14፡23) አንዳንድ ጊዜ ደግም ለብቻው ወደ እግዚአብሔር እየጸለየ ያድር ነበር። (ሉቃ. 6፡12) በዚህም ከላይ ባሰፈርነው ክፍል ከደቀ መዛሙርት መካከል አንዱ ጸሎትን እንዲያስተምራቸው ጌታን ሲጠይቀው እርሱ ከጸሎት ስፍራ እየተመለሰ ነበር። ጠያቂው ሁለት ነገሮችን ያስተዋለ ይመስላል። አንደኛው በጌታ የጸሎት ሕይወት ተደንቋል። ሁለተኛው የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ጸሎት እንደተማሩ እነርሱንም ጌታ ጸሎት እንዲያስተምራቸው ፈልጓል።

ጌታ ለዚህ ጥያቄ የሰጠው መልስ ሰለ ጸሎት እጅግ ብዙ የምንማርበት ነው። በዚህ ትምህርት ውስጥ በመጀመሪያ የምንመለከተው ትልቅ ቁብ ነገር ጸሎት በዋናነት የግንኙነት ጉዳይ እንደሆነ ነው። <u>የምንጸልየው ጠይቀን ለመቀበል ብቻ ሳይሆን፤ ጸሎት ወደ አባታችን የምንቀርብበትና ፊቱን የምንሻበት መንገድ ነው።</u> ልጅ ከአባቱ ጋር መሆን ደስ እንደሚለው፤ ልጅ ከአባቱ ጋር ለመሆን ብቻ ወደ አባቱ እንደሚጠጋ ሁሉ እኛም በጸሎት ስንቀርብ የምንጠጋው ፊቱን በመናፈቅ መሆን አለበት።

ስሊዚህ የጸሎት ትምህርት ዋናው ቁልፍ የአባትናትና የልጅን ግንኙነት ማወቅ ነው። ለዚህ ነው ጌታችን ስትጸልዩ "በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ..." ብላችሁ ጀምሩ ብሎ ያስተማረው። ስንጸልይ የምንጸልየው ወደ አባታችን ነው። የዚህ መሰረቱ ደግም በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን ያገኘነው የልጅነት ስልጣን ነው። (ዮሐ. 1፡12) ሐዋሪያው ጳውሎስም ሲጸልይ "በሰማይና በምድር ያለ አባትነት ሁሉ ከሚሰየምበት ከአብ ፊት እንበረከካለሁ" ይለናል። (ኤፌ. 3፡14-15) <u>ልጅነትን ተረድቶ በልጅነት መንፈስ ለጸሎት መቅረብ ትልቅ በረከት አለው።</u> ምድራዊ አባት ሁልጊዜ ለልጁ መልካም ነገር እንደሚያስብ እንዲሁ የሰማዩ አባታችን ይልቁን ለልጆቹ ሁልጊዜ የሚበልጥ መልካም ነገርን ያስባል። ስንጸልይ የእግዚአብሔርን አባትነት በመረዳትና እርሱ የአባትነት ሁሉ መሰረት መሆኑን በማመን መሆን አለበት። ይህም እግዚአብሔር የሕይወት ሁሉ ምንጭና ጀማሪ መሆኑን ማወቅ ነው። አባት የህልውና ምንጭ ነው። አባት መገኛ ነው። ስለዚህ አባታችን ሆይ ብለን ስንቀርብ አንድም በልጅነት መንፈስና ስልጣን ባለን ግንኙነት እየቀረብን ሲሆን፤ ሁለትም እርሱ የሁሉ መገኛና ምንጭ እንደሆነም እያመንንና እያወጅን ነው። (ይቀጥላል)